#Burien Forward Together

የBurien ከተማ አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች እርዳታ እና መልሶ ማቋቋም ድጋፍ መርሃ-ግብር (Small Business Relief & Recovery Grant Program) አሁን ክፍት ሆኗል!

የBurien ከተማ በኮቪድ-19 ምክንያት የንግድ ድርጅታቸውን በመዝጋታቸው ጉዳት የደረሰባቸውን አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች ለመርዳት የሚውል የገንዘብ ድጋፍ ዝግጁ አድርጓል። መስፈርቶቹንለሚያሟሉ የንግድ ድርጅቶች እስከ $5,000 የሚደርስ የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል። የገንዘብ ድጋፉ ውሱን ሲሆን ማመልከቻ የማቅረቢያ ጊዜውም ጁላይ 13 ቀን ያበቃል።

የገንዘብ ድጋፍ መርሃ-ግብሩ ግቦች፡

- አነስተኛየንግድ ድርጅቶች በራቸውን ክፍት አድርገው እንዲቆዩ መርዳት
- የምጣኔ ሃብትመልሶ መቋቋምንና ለችግር አለመበገርን
- የአካባቢ ሥራዎችን መጠበቅ
- ሌላ የገንዘብ ድጋፍ ዕድል ለማግኘት ለማይችሉ የንግድ ድርጅቶች እርዳታ ማቅረብ፡

መስፈርቶቹን የሚያሟሉ የንግድ ድርጅቶች ማሟላት ያለባቸው፡

- የBurien የንግድ ፈቃድ ሊኖራቸው ይገባል
- አምስት ወይም ከዚያ ቁጥር ያነሱ የሙሉ ሰዓት (ከሙሉ ሰዓት የሚመጣጠን) ሠራተኞች ያሉት
- በBurien ከተማ ውስጥ ከ12 ወራት ለበለጠ ጊዜ በሥራ ላይ የቆየ
- ከኮቪድ-19 ጋር በተገናኘ የሥራ መዝጋት ምክንያት ከ25% በላይ የሆነ የገቢ መቀነስ ያጋጠመው
- ለትርፍ የተደራጀ የንግድ ድርጅት መሆን
- ፍራንቻይዝ ወይም ብሄራዊ የንግድ ሰንሰለት ያልሆነ
- ከደሞዝ ጥበቃ ፕሮግራም (Paycheck Protection Program), ከ SBA የኢኮኖሚ ጉዳት አደጋ ብድር ፕሮግራም (Economic Injury Disaster Loan program), ከ SBA የኢኮኖሚ ጉዳት አደጋ ብድር የቅድሚያ (Economic Injury Disaster Loan Advance) (ግራንት)የገንዘብ ድጋፍ ያላገኘ ወይም በኮቪድ-19 ጋር ከተገናኘ ሌላ ፕሮግራም ከ$5,000 የበለጠ ገንዘብ ያላገኘ

የገንዘብ ድጋፍ መርሃ-ግብሩን እንዲያስተዳድር ቬንቸርስ ነንፕሮፊት (Ventures Nonprofit) በከተማው ተመርጧል።

ስለገንዘብ ድጋፉ የበለጠ ለማወቅ እና በኦንላይን ለማመልከት፡

venturesnonprofit.org/buriengrants

ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት ቬንቸርስ ነንፕሮፊትን (Ventures Nonpro it) ያግኙ፡

(206) 486-3733 • buriengrants@venturesnonprofit.org

Burien

Amharic